## በሚያዚያ (ኤፕሪል) 5, 2017 ላይ፣ የ KING COUNTY HOUSING AUTHORITY

## ለሼክሽን 8 የቤት ኪራይ እርዳታ ወረፋ ስም ዝርዝር **ለምደባ ማመልከቻዎችን መቀበል ይጀምራል**

- *ሁሉም ማመልከቻዎች በኦንላየን በ KCHA ድረ ገጽ [WWW.KCHA.ORG](http://WWW.KCHA.ORG)ላይ ከሚያዚያ (ኤፕሪል) 5, 2017 8 ጠዋት ጀምሮ እስከ ሚያዚያ (ኤፕሪል) 18, 2017 4 ከሰዓት ድረስ መግባት አለባቸው።*

- *ከሚያዚያ (ኤፕሪል) 18ኛ ቀን በኋላ፣ በዕጣ ለመመደብ ከወረፋው የስም ዝርዝር ላይ ዕጣ ይወጣል። ዕጣ የወጣላቸው የመጀመሪያዎቹ 3,500 ስሞች ብቻ በወረፋው የስም ዝርዝር ላይ ቦታ ያገኛሉ።*

- *ማመልከቻን በመጀመሪያው ቀን ላይ ማስገባት የሚያስገኘው የተለየ ጥቅም የለም።*

- *ከአንድ ቤተሰብ አንድ ማመልከቻ ብቻ ነው ተቀባይነት የሚኖረው።*

- *አመልካቾች ለመሳተፍ የሚከተለውን በሙሉ ያሟሉ መሆን ይኖርባቸዋል፥*
  - *የቤተሰቡ አስተዳዳሪ ከ 18 ዓመት በላይ መሆን ይኖርባቸዋል።*
  - *ቤተሰቡ ቢያንስ አንድ በአካል የታጎለ፤ ወይም ቢያንስ አንድ የ 62 ዓመት ዕድሜ፤ ወይም ከ 18 ዓመት ዕድሜ በታች የሆነ አባል ያለው መሆን አለበት።*
  - *የቤተሰቡ ገቢ አነስተኛ መሆን አለበት።*
  - *የቤተሰቡ ገቢ ከ 30 በመቶ ወይም ከአማካይ የገቢ መጠን ያነሰ መሆን፤ ወይም ቤት አልባ መሆን፣ ወይም ከመመዘኛ ደረጃ ዝቅተኛ በሆነ መኖሪያ ቤት ውስጥ የሚኖር መሆን፤ ወይም ለኪራይና ለዩቲሊቲ (መብራት፣ ውሃ፣ ወዘተ) ከገቢው ከ 50 በመቶ በላይ የሚከፍል መሆን አለበት።*
  - *በአጠቃላይ፣ ቤተሰቡ በአሁን ሰዓት በመንግስት የተደገፈ የመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚኖሩ መሆን አይችሉም።*

- *የሓሰተኞች ማስጠንቀቅያ፥ ይህን ማመልከቻ ለመሙላት እርዳታ እንሰጣለን ብለው የሚያስከፍሉ ከሆነ፣ የሓሰት ድርጅቶች ናቸው። የማመልከቻው ሂደት በነጻ ሲሆን የሚያገኙት በድረ ገጽ ብቻ ሊሆን ይገባል። የወረፋ መዝገብ ላይ በእርግጠኝነት እናስመዘግባለን ለሚሉ ድርጅቶች በጭራሽ እንዳይከፍሉ። እንደዚያ የሚሉ ድርጅቶች ከገጠሞት፣ እባክዎን ለ King County Housing Authority የሓሰት ምርመራ ክፍል በ 206-214-1353 ይደውሉ።*